# ምርመራ ማድረግ ያለብኝ መቼ ነው? አለም አቀፋዊ ጉዞ

## ጽሁፍ

[አነቃቂ ሙዚቃ]

[ትረካ]

የ COVID-19 ምርመራ ማድረግ ያለብዎት መቼ ነው?

ቤተሰብዎ ወደ ሌላ ሃገር ጉዞ እያደረገ ነው። CDC ከጉዞ በፊት እና በኋላ ምርመራ እንዲያደርጉ ይመክራል። በጣም ወቅታዊ የሆኑ መስፈርቶችን እና የጉዞ ምክሮችን ለማግኘት የ CDC ን ድህረ ገጽ (https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/travelers/international-travel-during-covid19.html) ይጎብኙ።

አንዳንድ አገሮች ከመጓዝዎ በፊት እንዲመረመሩ ወይም እንዲከተቡ ሊጠይቁ ይችላሉ። የራሱዎን ልዩ የጉዞ መድረሻ መስፈርቶች ማረጋገጥዎን እርግጠኛ ይሁኑ። (https://travel.state.gov/content/travel/en/traveladvisories/COVID-19-Country-Specific-Information.html)

በተጨማሪም፣ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በሚመለሱበት ጊዜ፣ ሁሉም ተጓዦች ጉዞ ከመደረጉ **አንድ** ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የተደረገውን አሉታዊ(ነገትቭ) የCOVID-19 ምርመራ ማሳየት **አለባቸው**።

ከታመሙ ወይም ለ COVD-19 ፖዘቲቭ ምርመራ ካደረጉ እና ከተመረመሩ ወይም ምልክቶችን ካሳዩ ገና 10 ቀናት ካልሆንዎት ጉዞ አያድርጉ።

በቅርቡ COVID-19 ካለበት ሰው ጋር የቅርብ ግንኙነት ከነበረዎት ጉዞ አያድርጉ። ከተጋለጡ ከአምስት ቀናት በኋላ ይመርመሩ እንድሁም የለይቶ ማቆያ እና የ 10-ቀን የማስክ ጊዜዎን እስኪጨርሱ ድረስ ጉዞ አያድርጉ።

የ COVID-19 ምርመራ ውጤትዎን እየጠበቁ ከሆነ ጉዞ አያድርጉ። በመዳረሻዎ ላይ እያሉ የምርመራ ውጤትዎ ፖዘቲቭ ሆኖ ከመጣ፣ ማግለልዎን ለማቆም አስተማማኝ እስኪሆን ድረስ ራስዎን ማግለል እና መመለሻዎን ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ ያስፈልግዎታል። ቤተሰቦችዎ እና የቅርብ ንክኪዎችዎ እንዲሁ ማግለል ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

ሁሉንም የተመከሩ የ COVID-19 ክትባቶች ካልወሰዱ፣ አለም አቀፋዊ ጉዞ ማድረግ የለብዎትም። መጓዝዎ የግድ ከሆነ፣ ከጉዞዎ ከሶስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከመነሻ ጊዜዎ በተቻለ መጠን አስቀድመው ምርመራ ያድርጉ።

በዚህ ሁኔታ፣ ቤተሰብዎ እሮብ ላይ ይወጣሉ። ሁሉንም የተመከሩ የ COVID-19 ክትባቶች ያልወሰዱ ሁሉም የቤተሰብ አባላት ከጉዞዎ በፊት እሁድ፣ ሰኞ፣ ወይም ማክሰኞ ሊመረመሩ ይገባል።

በተጨማሪም፣ ባለፉት 90 ቀናት ውስጥ በ COVID-19 መያዙ እስካልተረጋገጠ ድረስ *ሁሉም ሰው* አለም አቀፍ ጉዞ ካደረጉ ከሶስት እስከ አምስት ቀናት ***በኋላ*** መመርመር አለበት ።

እርስዎ እና ቤተሰብዎ አርብ ላይ ከጉዞው ይመለሳሉ። ሁላችሁም ሰኞ፣ ማክሰኞ፣ ወይም እሮብ ምርመራ ማድረግ አለባችሁ። ምልክቶች ከታዩብዎት፣ ወዲያውኑ ይመርመሩ።

ሁሉንም የተመከሩ የ COVID-19 ክትባቶች ያልወሰዱ ተጓዦች እንዲሁም ከአለም አቀፍ ጉዞ በኋላ ለ5 ቀናት በቤት ውስጥ (ለይቶ ማቆያ) መቆየት አለባቸው። ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ ሁሉንም የተሞከሩ የ COVID-19 ክትባቶችን የወሰዱ ወይም COVID-19 የያዛቸው ሰዎች ማግለል አያስፈልጋቸውም።

በሌሎች ጊዜዎች መመርመር እንዳለብዎት እና የት እንደሚመረመሩ የበለጠ መረጃ ለማወቅ የMDH CPVID-19 መመርመሪያ ድህረ ገጽን ይጎብኙ።
(https://www.health.state.mn.us/diseases/coronavirus/testsites/index.html)

[አነቃቂ ሙዚቃ]

Minnesota Department of Health
Communications Office
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-4989
health.communications@state.mn.us
www.health.state.mn.us

2/2/22 (Amharic)

*ይህን መረጃ በተለያየ ቅርጸት ለማግኘት፣ በሚከተለው ይደውሉ፦ 651-201-4989*